# ሁለገብ አመጽ ወይም ግዞት!

### መለስ ዜናዊ በምርጫ ስም ፈላጭ ቆራጭ ዘውድ-ቀረሽ ንጉስ ሆኗል፤
### ለዴሞክራሲ የተጀመረው ትግል ከዚህ ወዴት?

ተስፋ በመሰረቱ ጥሩ ነገር ነው። የማይጨበጥ ተስፋ ግን አደገኛ ነው። ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ሊፈጽሟቸው የሚገባቸውን አንገብጋቢ ውሳኔዎች ከማድረግ ያግዳቸዋልና። ፍዝዝ ብለው የማይሆነውን ሲጠብቁ ቀን ይጨልማል። በዚህ ምክንያት የማይጨበጥን ተስፋ ከሞኝነት ልንቆጥረው እንችላለን። ብዙ ጊዜም ተስፋና ሞኝነት እየተወናበዱ መዘናጋት ይሆናል።

በዚህ ሳምንት፣ በኢትዮጵያ አንድ ትልቅ ፖለቲካዊ ክስተት ተከናውኗል። እሁድ እለት የተካሄደው የምርጫ ተውኔት፣ "ዴሞክራሲ ሂደት ነው" እያሉ የወያኔን አምባገነናዊነት ሲያደባብሱለት የነበሩትን የምእራብ አገር መንግስታት ሳይቀር አስደንግጧል። አሁን ምንም ምክንያት ሊፈጥሩለት የማይችሉት ነገር ሆነባቸው። እየጨነቃቸውም ቢሆን እየወጡ ዘረኛውን አገዛዝ ማውገዛቸውን ቀጠሉ።

ሌሎች ገለልተኛ ሃይሎች ከዳር እስከዳር የምርጫ ተብየውን አስቂኝነት እና የመለስን ከመንግስቱ ሃይለማርያም ብሶ መገኘት ሲያወሱ ቆይተዋል። በርካታ ኢትዮጵያውያን ለግንቦት 7 ንቅናቄ በተለያዩ መንገዶች በሚያደርሱት መልክት ደግሞ፤ "'ወያኔ እያለ እውነተኛ ምርጫ አይካሄድም' ያላችሁት ተረጋገጠ፤ 'ትግሉ ወያኔ ሁሉን ነገር ለራሱ እንዲመች አድርጎ ባመቻቸው ሁኔታ ለምርጫ መዘጋጀት ሳይሆን የምርጫ ሜዳውን ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲስማማ አድርጎ ማዘጋጀት ነው' ያላችሁት ተረጋገጠ፤ በዚህ ምርጫ አሸናፊው ግንቦት 7 ነው" ይሉናል። እኛ እንደሆን ግንቦት 7 ከመመስረቱም በፊት ወያኔ ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ አይገዛም ሲል የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ አሸንፏል፤ አርቆ አሳቢነቱ እና አዋቂነቱ ምስክር አግኝቷል ባዮች ነን።

የተከሰተው ነገር ግልጽ ነው፤ ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ህዝብ በነጻነት ውሳኔ እንዲሰጥ ለመፍቀድ እና ለዛም ውሳኔ ለመገዛት ዝግጁ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን የማይችል ፍጡር መሆኑ ዳግመኛ ተረጋግጧል። ኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ ምድር፤ የአንድ አምባገነን መፈንጫ መሆኗም፣ ለሁሉም ከጥርጥር ባሻገር ያለ ሃቅ ሆኗል። አሁን ያለው ጥያቄ ይኸን እብሪተኛ አገዛዝ እንዴት አድርጎ ማስወገድ ይሻላል የሚለው ብቻ ሆኗል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ገና ከ1997 ምርጫ በፊት የቅንጅት መሪዎችን፥ "ለመሆኑ ይህ አገዛዝ በምርጫ ስልጣን ይለቃል ብላችሁ ነው?" ብሎ ሲጠይቅ የነበረው ህዝብ፤ ዛሬ የባሰ ጉድ በታየ ማግስት ይታለላል የሚል እምነት የለንም። ሆኖም ግን መጪው ግዜ በውዥንብር የተሞላ ሊሆን ስለሚችል አንዳንድ ነገሮችን ካሁኑ አጥርቶ መሄዱ ይበጃል እንላለን።

ዋናዎቹ የውዥንብር መነሻዎች በዚህ ሳምንት ብቅ ብለው የምናያቸው ሁለት ጉዳዮች ናቸው። የድጋሚ ምርጫ ጥሪ እና ምራባዉያን አገራት በወያኔ ላይ ያኖሩት ውግዘት። ተቃዋሚዎች የድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ እያደረጉ ያሉትን ጥሪ በሚመለከት ያናገርናቸው የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፥ "የምርጫው ችግር በምርጫ እለት ወይም፣ ከምርጫው በፊት ጥቂት ቀናትና ወራት ቀደም ብሎ የተከሰተ አይደለም። የምርጫው ችግር በህገ-መንግስቱ ምርጫን በሚመለከት ከተጻፉት አንቀጾች ጋራ የተሳሰረም አይደለም። ባለፉት ሃያ አመታት የተካሄዱት ምርጫዎች ችግር፣ ከወያኔ መሰረታዊ ጸረ-ኢትዮጵያዊነት እና ጸረ-ዴሞክራሲያዊነት የሚመነጭ ነው" ብለውናል። በርግጥም፥ አቶ አንዳርጋቸው እንዳሉት የምርጫው ተውኔት ስለተደገመ ብቻ ምርጫ አያደርገውም ወደሚለው ድምዳሜ ለመድረስ ብዙም ምርምር አያሻውም።

ምእራባውያኑ በወያኔ አገዛዝ ላይ የሚያቀርቧቸውን ውግዘቶች በተመለከተ፥ ስላልተስተካከለው የፖለቲካ ሜዳ መናገር የጀመሩት ዘረኛው አምባገነን መለስ የፓርላማ መቀመጫውን ሙሉ በሙሉ መውሰዱ ከታየ በኋላ እንደሆነ ልብ ይሏል። ከዛ ቀደም፥ በተለይ የአሜሪካው አስተዳደር፣ በራሱ ህዝብ ተወካዮች ሳይቀር አንድ ነገር እንዲናገር ተማጽኖ ሲቀርብለት ቆይቷል። መለስ ይህንን ዱብ እዳ አውርዶ ባያሳፍራቸው እና አንድ ሃምሳ መቀመጫዎችን ለተቃዋሚዎች ሰጥቶ ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባትም ምእራባውያኑ በምርጫ 97 ወቅት እንዳደረጉት፣ ዝም ዝም፣ ሁሉም ዝም ይሆን ነበር።

አሁንም ቢሆን፣ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ "እሺ አንዳንድ መሻሻሎችን አደርጋለሁ" ብሎ ቢስማማ እና ምእራባውያኑ ቢቀበሉ፣ ጊዜ መግዣ እንጂ እውነተኛ ለውጥ የሚመጣበት መንገድ አይሆንም። ይህን ስንል፤ መንግስታቱ የሚሉት ነገር ዋጋ የለውም ለማለት አይደለም። ይልቁንስ፥ አንደኛ፦ ዘረኛውና አምባገነናዊው አገዛዝ እስካለ ድረስ፣ ሊደረግ የሚችለው ማንኛውም ለውጥ እውነተኛ ለውጥ ሊሆን አይችልም። ሁለተኛ ደግሞ፥ በአገራችን ውስጥ ዋናዎቹ የለውጥ አከናዋኞች እኛው ኢትዮጵያውያን ብቻ ነን። ምእራባውያን ዘረኛውን አምባገነን በማጠናከር የትግላችንን ዘመን ማራዘሙን በማቆም አስተዋጾ ሊያደርጉ ይችላሉ እንጂ ነፃ ሊያወጡን አይችሉም። ያ በመሰረቱ እውነተኛ ነፃነት ሊሆንም አይችልም። በገዛ እጣ ፈንታችን ላይ ባለቤትነታችንን ልናውጅ ይገባል።

ስለዚህም፥ የዳግም ምርጫ ወሬውም ሆነ የምእራባውያን ንግግር የማይጨበጥ ተስፋ እየመገበ እንዳያዘናጋን እንጠንቀቅ። አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን፥ "ዳግም ምርጫ አያስኬድም ካሉ፣ ታዲያ ምን ይሻላል?" ብለናቸው ነበር። "ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የማስፈኑ መሰረታዊ ችግር ወያኔ ራሱ መሆኑን ተረድተው፣ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታም ውስጥ የሚገኙት ድርጅቶችም ጭምር፣ ወያኔ የሚወገድበትን ሁኔታ ባስቸኳይ ለመፍጠር ተደጋግፈው የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ብቻ ነው። ሌላ ቀላል አማራጭ ቢኖር ደስ ባለን ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ በነጻ ምርጫ የሚሰይመውን መንግስታዊ ስርአት ለመመስረት ወያኔን ከስልጣን ከማስወገድ ሌላ ምንም አቋራጭ መንገድ የለም።" ብለዋል።

ጨምረውም፥ "የየድርጅቶቹ ወያኔን የማስወገጃ የትግል ስልት ያሰኘው መሆን ይችላል። ሰላማዊ ህዝባዊ እምቢተኛነትን ከማቀጣጠል አንስቶ፣ መሳሪያ አንስቶ እስከመፋለም ድረስ። ነገር ግን ሰላማዊ እምቢተኛነትን ማቀጣጠል ማለት የመለስን ፈቃድ እና ቡራኬ እየተጠበቀ ሊሰራ የማይችል፤ ጠመንጃ ከሚያነሱትም በላይ የደፋሮች ደፋርን የሚጠይቅ ስራ መሆኑን ጠንቅቆ ባወቀ መንገድ የሚፈጸም ነው።" ሲሉ አስተያየታቸውን ቋጭተዋል።

እንግዲህ ሁለት ትላልቅ አማራጮች ብቻ ግልጽ ሆነው ይታያሉ፦ ሁሉንም አይነት አመጽ ወይም ባርነት።

***ይህ ጽሁፍ በግንቦት 7 ድምጽ ራድዮ ግንቦት 21 ቀን ከተላለፈው ስርጭት የተወሰደ የዜና ትንታኔ ነው። አስተያየቶቻችሁን በ*** g7radio@ginbot7.org ***እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን።***